# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ቁጥር 107 ሰኔ 3 ቀን 2002 ገጽ 1


ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

**የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ**

**“የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:” የሚል ነው።**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው**

## ለኢትዮጵያ የሚድያ አውታሮች በሙሉ

### ከግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ጽ/ቤት

### የሰኔ 1 1997 ዓ.ም የዴሞክራሲ ሰማእታትን በሚመለከት የተላለፈ መልእክት ሰኔ 1 2002 ዓ.ም

ዛሬ ሰኔ 1 ቀን ነው:: የዛሬ 5 አመት በእዚህ እለት በምርጫ የሰጠነው ድምጻችን ይከበር በማለት በሰላማዊ መንገድ ጥያቄ ለማቅርብ በወጡ የሃገሬው ዜጎቸ ላይ የመለስ ዜናዊ አምባገነናዊ አገዛዘ በወሰደው አረመኒያዊ የእመቃ እርምጃ ከ40 በላይ የሚሆኑት ህይወታቸው አልፏል። በሽህ የሚቆጠሩ ዜጎችም አሰቃቂ ቅጥቀጣና የወህኒ እጎራ ተፈጽሞባቸዋል።

ይህን እለት እነዚህን የዴሞክራሲ ሰማእታት አስበን የምንውልበት ነው:: እለቱን እያስታወሱም በሃዘን ለሚሰቃዩ የቅርብ ቤተሰቦቻው፣ ዘመዶቻቸውና እውቆቻቸው እኛም ሰማእታቱን ያልረሳናቸው መሆኑን የምንግልጽበት እለት ነው::

እለቱ ሰማእታቱ የወደቁለትን የዴሞክራሲ ሰንደቅ ከፍ አድርገን በማውለብለብ ዛሬ በሃገራችን ላይ የሰፈነውን አምባገነናዊ አገዛዘ፣ ህዝብ በነጻነቱ በመረጠው መንግስታዊ አስተዳደር እንዲተካ በማድረግ ሰማእታቱን ለዘላለሙ ህያው ለማድረግ ቃል የምንገባበትነው። የወደቁት ህዝብ በነጻ የምርጫ ድምጹ የሚሾመውና የሚሸረው ፈሪሃ ህዝብ የሚሰማው መንግስት በኢትዮጵያችን ለማየት ነውና።

በሃገር ውስጥም ሆነ ከሃገር ውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በሙሉ እነዚህን ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም በግፍ የተጨፈጨፉ ወገኖቻችንን አብረውን እንዲያስታውሷቸውና የወደቁለትንና የሁላችንም የሆነውን በሃገር ዴሞክራሲ የማስፈን ምኞታቸውን ከግብ ለማድረስ በጋራ እንድንነሳ ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ወገናዊ ጥሪውን ያቀርባል::

**ዘላለማዊነት ለሰማእታቱ!!!**
**ክስመት ለአምባገነንነት!!!**

**ከግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ጽ/ቤት**

## የወያኔ ጦር የወታደሮች ፍልሰት ችግር እንዳለበት ታወቀ

የወያኔ ጦር ከፍተኛ የሆነ የወታደሮች ፍልሰት ችግር እንዳለበት የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ከኢትዮጵያ በላከው ዘገባ አስታውቋል።

ዘጋቢያችን ከሰሜን ኢትዮጵያ ባስተላለፈው መረጃ፣ በሰሜን ምእራብ ኢትዮጵያ በጠገዴ ወረዳ በተለያዩ ቀበሌዎች ተሰማርቶ የነበረው የ4ኛ ሻለቃ ልዩ ሃይል በደረሰበት የወታደሮች ፍልሰት በመዳከሙ አገዛዙ በአዲስ ምሩቆች ሊሞላው ተገዷል። አብዛኞቹ ወታደሮች በክህደት እንደሚለቁ የታወቀ ሲሆን፤ የተቀሩት በምግባረ ብልሹነት ሰበብ እንደሚባረሩም መረጃው አስረድቷል። የወያኔ አገዛዝ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ይደግፋሉ ብሎ የሚጠረጥራቸውን ወይም ለዘር አድሎ አሰራሩ ምቹ ሆነው ያልተገኙትን የጦር አባላት በምግባረ ብልሹነት እያሳበበ የማባረር የቆየ ልምድ እንዳለው ይታወቃል።

የወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ጦር ወደ ሰሜን ምእራብ ኢትዮጵያ ማጓጓዝ መጀመሩን ቀደም ብለን ዘግበናል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ አገዛዙ ልዩ ሃይል የሚባል አዲስ ሰልጣኝ ጦር አስመርቆ ከግንቦት 22 ቀን 2002 አመተ ምህረት ጀምሮ በተለያዩ ሰሜናዊ የአገሪቱ ወረዳዎች እያጓጓዘ መሆኑ ታውቋል። ከሁለት መቶ በላይ የሚሆኑ አዲስ ምሩቃንም በጠገዴ የተዳከመውን የ4ኛ ሻለቃ ልዩ ሃይል እንዲያጠናክሩ መመደባቸውን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አስረድቷል።

በጦሩ ውስጥ ከሚካሄደው የዘር አድሎ እና ሌላም ኢ-ፍትሃዊ አሰራር የተነሳ በርካታ አባላቱ በየጊዜው እንደሚኮበልሉ ይታወቃል። እስካሁን የታየው ፍልሰት ግን በጦሩ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የሚንጸባረቀውን ቅራኔ እንደማይገልጽ እና እድሉን ቢያገኙ በሺዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች እንደሚከዱ ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ ሰዎች ይናገራሉ።

## በኬንያ የኢትዮጵያ ኤምባሲ የተሾመች ግለሰብ የወያኔ ዘረኛ ፖሊሲ ተጠቃሚ ነች ተባለ

በኬንያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ የኢሚግሬሽን ካውንስለር ሆና በቅርቡ የተመደበችው ግለሰብ ለስራው የሚያስፈልገውን ብቃት የሌላት እና የወያኔ አገዛዝ ዘረኛ ፖሊሲ ተጠቃሚ ነች ሲሉ የኤምባሲው ምንጮች ስሞታ አሰምተዋል።

ለግንቦት 7 ድምጽ ከስፍራው የደረሰው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ አለም ተክሉ የተባለችው ግለሰብ የወያኔ የቀድሞ ታጋይ ስትሆን፣ የተማረችው እስከ ሶስተኛ ክፍል ድረስ ብቻ ነው። ኤምባሲው ኬንያን ጨምሮ ለታንዛኒያ፣ ማላዊ እና ማዳጋስካር አገልግሎት የሚሰጥ እንደመሆኑ ከፍተኛ ሃላፊነት ያለበት ነው። አለም ተክሉ የተመደበችበት ሃላፊነት ከነዚህ አራት አገራት ወደ ኢትዮጵያ ለመጓዝ ቪዛ ከሚፈልጉ ሰዎች ጋር የሚያገናኛት ቢሆንም፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መናገር እንደማትችል ምንጮቻችን ገልጸዋል።

አለም ተክሉ ለዚህ ስራ በየወሩ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ የአሜሪካን ዶላር እንደሚከፈላት እና ይህም ከሌሎች ተነፃፃሪ ሃላፊነት ካላቸው የኤምባሲ ሰራተኞች ክፍያ ጋር ሲወዳደር እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ ታውቋል። እሷ በኤምባሲው በተመደበችበት ሰሞን፣ ሁለት ኦሮሞ የሆኑ የኤምባሲው ነባር ሰራተኞች ባልታወቀ ምክንያት ከስራቸው ተባረዋል። እነዚህ ግለሰቦች ለነበራቸው ሃላፊነት ብቃት እንዳላቸው አስመስክረው የተቀጠሩ ሲሆን፤ የአንደኛው የወር ደሞዝ 465 የአሜሪካ ዶላር፣ የሌላኛው ደግሞ 410 የአሜሪካ ዶላር ነበር።

## ፍሪደም ሃውስ የወያኔ አገዛዝ የዘር አድሎ ይፈጽማል፤ በኢትዮጵያ ያለው አፈናም ከቀደመው አመት የከፋ ሆኗል አለ

ፍሬደም ሃውስ የተባለው አንጋፋ አለም አቀፍ የነፃነት ተሟጋች ድርጅት ሰሞኑን ባወጣው አመታዊ ሪፖርት የወያኔ አገዛዝ የዘር አድሎን በሰፊው እንደሚፈጽም፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሁኔታ ከቀደመው አመት የከፋ መሆኑን ገልጿል።

ተቋሙ የወያኔ አገዛዝ በኢኮኖሚ እና በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ የዘር አድሎ እንደሚፈጽም እና ከትግራይ ለሆኑ ሰዎች እንደሚያደላ ተናግሯል። በሌሎች ብሔረሰቦች ላይም በሰፊው አድሎ እንደሚፈጸም መስክሯል።

ፍሪደም ሃውስ የወያኔ አገዛዝ በሲቪል ተቋማት ላይ የሚያካሄደውን አፈና፣ ጸረ-ሽብር ተብዬውን ህግ፤ እንዲሁም በተቃዋሚዎች ላይ የሚደርሰውን ግፍ እንደምክንያት በመጥቀስ በኢትዮጵያ ያለው የፖለቲካ ነፃነት ሁኔታ ከቀደመው አመት የከፋ መሆኑን ገልጿል። የወ/ት ብርትኳን ሚደቅሳ እስር፤ አገዛዙ የሚጠቀምባቸው የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ከሞላ ጎደል የመረጃ ሜዳውን መቆጣጠራቸው፤ የብዙ ነፃ ሚድያ ድርጅቶች መዘጋት እና በተቀሩት ላይ የሚደርሰው አፈና በሪፖርቱ ውስጥ ተጠቅሰዋል።

ፍሪደም ሃውስ በዚሁ ሪፖርቱ፣ በኢትዮጵያ የትምህርት ወይም አካደሚክ ነፃነት የተገታ እንደሆነ ጠቅሷል። የወያኔ አገዛዝ ትምህርት ቤቶች ለተቃዋሚዎች ቅርብ ናቸው በሚል እንደሚከስ እና በቅርብ እንደሚቆጣጠራቸው ተናግሯል።

ተቋሙ ኢትዮጵያን በከፊል ነፃ ከሚባሉ አገሮች ቡድን ውስጥ የመደበ ቢሆንም፤ ይህ ሪፖርቱ የተጠናከረው ግን በርካቶች ኢትዮጵያን የአንድ ፓርቲ አገር ብለው የፈረጁበት የግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት ከመካሄዱ በፊት ነበር።

## ሽምግልና ተዋረደ!!!

ሽምግልና ተዋረደ!!! ራሳቸውን “የሃገር ሽማግሌ” ብለው በሚጠሩ የመለስ ዜናዊ ተላላኪዎች ምክንያት ሽምግልና ረከሰ!!! ሽምግልና በደልን ማርዘሚያ ሆነ!!!

ሽምግልና አያት፣ ቅድመ-አያቶቻችን አዳብረው ያቆዩልን እጅግ የተከበረ ማኅበራዊ ተቋም ነው። ሽምግልና ተደጋግፎ ለመኖር፤ ግጭቶችን ለመቀነስ እና ፍቅርን ለማብዛት ማኅበረሰባችን በብዙ ምዕተ ዓመታት ልምድ ያዳበረውና ሞገስን የቸረው በየጊዜውም እያሻሻለው የሚሄድ ማኅበራዊ እሴት ነው።

ለሽምግልና መብቃት ክብርም ኃላፊነትም ነው። ለሽምግልና ለመብቃት ከእድሜ መብሰልም በላይ የበርካታ ክህሎቶችና ባህሪያት ባለቤት መሆንን ይጠይቃል። የፀጉር መሸበት፣ ነጠላ መልበስና ጭራ መያዝ ወይም “ሽማግሌ ነኝ” ብሎ ራስን መሾም ሽማግሌ አያሰኝም።

ለሽምግልና ለመብቃት ለእውነት መቆም ይጠይቃል። ለሽምግልና ለመብቃት ፍትህን መረዳት፤ ለፍትህ ጥብቅና መቆምን ይሻል። ለሽማግልና ለመብቃት የተበዳይን ህመም መታመምን ይጠይቃል። ለሽምግልና ለመብቃት ቅራኔዎችን የመፍታት ጥበብን ማወቅ ግድ ይላል። ለሽምግልና የሚመረጥ ነው እርቅን የሚሻ ቢሆንም ለእርቅ ብሎ ለጉልበተኛው የሚያዳላ መሆን የለበትም። ይህን ካደረገማ ከጉልበተኛው ሎሌ ምን ለየው? ለሽምግልና የሚመረጥ ሰው ታጋሽ፣ አድማጭ፣ አርቆ አስተዋይና አንደበተ ርቱዕ መሆን ይገባዋል። አጥፊን “አጥፍተሃል” የማለት ድፍረት የሌለው ሰው ሽማግሌ አይሆንም። እውነት ለመናገር የማይደፍር ሰው ምን ፀጉሩ ቢሸብት “ሽማግሌ” አይባልም። የበዳይ ተላላኪ “ሽማግሌ ነኝ” ቢል ከልቡ “አዎን” የሚለው አያገኝም። ሽምግልና ውስብስብ፣ ሰፊና ጥልቅ የሆነ ባህላዊና ማኅበራዊ ጥበብ ነው።

ወያኔ ኢትዮጵያዊያን በምናከብረው ነገር ሁሉ ላይ መዝመት ዓላማው ነው። ሽምግልና ኢትዮጵያዊያውያን ከምንኮራበት እሴት አንዱ ነውና ዘምቶበታል። እናም “የሃገር ሽማግሌዎች ኮሚቴ” የተባለ የሽምግልና ማዋረጃ ተቋም ገንብቶብናል። በዚህ ኮሚቴ አማካይነትም የተከበረውን ሽምግልናን አዋርዷል፤ እያዋረደም ነው።

መለስ ዜናዊ ገድሎ፣ ገርፎ፣ ደብድቦ ሲበቃው ተላላኪዎቹን “ሽማግሌዎቹን” ይልካል - እንዲያስታርቁት። ታድያ “ሽማግሌዎቹ” መለስ ላከን አይሉም። “በራሳችን ተነሳሽነት ሽምግልና ጀመርን” ብለው ይዋሻሉ። ሥራቸውን በመዋሸት ጀምረው በመዋሸት ይጨርሳሉ።

የኮሚቴው ጭንቅላት አሜሪካ ይኖራል። መለስ ዜናዊ ተንኮል በሸረበ ቁጥር ይኸን ሽምግልናን አዋራጅ ከአሜሪካ እየጠራ፤ ሸራተን አልያም ሂልተን ሆቴል እያስቀመጠ አገር ውስጥ ካሉት አባሎቹ ጋር በኛ ስቃይ “ሽምግልናን” እንዲተውኑ ያደርጋል። እነሱም ሽምግልናን ያረክሳሉ፤ ስቃያችንንም ያረዝማሉ።

እነዚህ “የሃገር ሽማግሌ” ተብለው በመለስ ዜናዊ የተሾሙ ሰዎች ዋነኛ ተልዕኮ ተበዳዮች በደልን አሜን ብለው እንዲቀበሉ ማግባባት ነው። የበደሉን ዓይነት ለመመርመር አቅሙም ፍላጎቱም የላቸውም። ተበዳዮችን ይቆጣሉ፣ ያግባባሉ፣ ይለማመጣሉ። በዳይን ግን ይታዘዛሉ፤ ለበዳይ ይላላካሉ። እንዲህ ዓይነት ሽምግልና የለም። ይህ ሽምግልናን መስደብ ነው።

ይህ የሽማግሌዎች ቡድን በቅንጅት መሪዎች መፈታት ወቅት የገባውን ቃል በማፍረስ ክህደት ፈጽሟል። እውነትን ለመናገር ባለመድፈሩ ለወ/ት ብርቱካን ሚደቅደሳ ዳግም እስርና እንግልት ምክንያት ሆኗል። ቡድኑ ከመለስ ዜናዊ ፈቃድ ውጭ መተንፈስ እንኳን የማይችል ግዑዝ እቃ ነው። ኢትዮጵያዊያን በዚህ እኩይ ቡድን ተግባራት ምን ያህል እንዳዘንን መግለጽ ያዳግታል።

የዚህ ሽምግናን እያዋረደ ራሱን “የሃገር ሽማግሌዎች ኮሜቴ” ብሎ የሚጠራው ቡድን አንዱ አባል ከውሸት ሽምግልና በተጨማሪ የእምነት ተቋም መሪነትንም ካባ አጥልቆ ያጭበረብራል። በመንግሥት ጋዜጠኛና ካሜራ እየታገዘ የቃሊቲውን የሰቆቃ እስር ቤትን “የአፍሪቃ ምርጥ እስር ቤት” የሚስያብል ፊልም አሰርቶ ለዜና እይታ አብቅቷል። በዚህ ውሸት “ሽምግልናውን” ብቻ ሳይሆን የሚመራውን የእምነት ተቋምንም አርክሷል።

መንግሥቱ ኃይለማርያም ከሰራቸው ግፎችም እብደቶችም አንዳችም እንዳይቀርበት፤ እንዲያውም ከዚያ በላይ ለማስመስዝገብ በብርቱ የሚጥረው መለስ ዜናዊ ሰሞኑን ፓርላማ ተብየውን በራሱ ሰዎች ብቻ መሙላቱ ይታወቃል። ይህ ተግባር ኢትዮጵያዊያንን ብቻ ሳይሆን አፍሪቃዊያንን ሁሉ እያሳፈረ ባለበት ባሁኑ ወቅት እፍረት የለሾቹ ሽማግሌዎች “ይህ አግባብ ነው ብላችሁ ተቀበሉ፤ መለስ ዜናዊንም አበጀህ በሉት” ለማለት ተፍ ተፍ ማለት ጀምረዋል። መለስ ይደነፋል። “ሽማግሌዎቹ” ተበዳዮች በደልን እንዲረሱ ብቻ ሳይሆን በዳዩን “አበጀህ” እንዲሉት በመማፀን ላይ ናቸው።

እነዚህ ሽምግልናን እያዋረዱ ያሉት “ሽማግሌዎች” የመለስን ትዕዛዝ እንጂ የሕዝብን አቤቱታ ሰምተው አያውቁም። የቅንጅት መሪዎች የተፈቱበት አግባብ ከእነሱ በላይ የሚያውቅ የለም። ወያኔ ውል አፍርሶ የንፁሃኑን ስም ሲያጠፋ ሰምተው አላስቆሙም። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በተናገረችው ውስጥ ውሸት እንደሌለ ከማንም በላይ እነሱ ያውቃሉ። ሆኖም ሕይወቷ አደጋ ውስጥ በወደቀበት ወቅት እንኳን እውነቱን የመነገር ድፍረት አላገኙም። ይህ ትብዝት በቀላሉ የሚፋቅ ይመስላቸው ይሆን?

አሁን በመለስ ዜናዊ ስለታዘዙ “የምርጫውን ውጤት ተቀበሉ” እያሉ ተቃዋሚዎችን መወትወት ቀጥለዋል። ደጋግሞ ቃሉን ያፈረሰ አካል አሁን እንደምን ሊታመን ይችላል? “የሃገር ሽማግሌዎች ኮሚቴ” ተብየው አጭበርባሪ ቡድንን ማመን ማለት ራሱ መለስ ዜናዊን ማመን ማለት ነው። መለስ በቃሉ ረግቶ የማያውቅ ቃለ አባይ ነው። “የሃገር ሽማግሌዎች ኮሚቴም” በቃሉ ረግቶ አያውቅም። የተቃዋሚ ፓርቲዎች አመራሮች በእነዚህ ሃሳዊያን እንደማይታለሉ ተስፋ እናደርጋለን።

ሽምግልና የምናከበርው ባህላችን ነው፤ መለስ ዜናዊ እና ውሸታም ሽማግሌዎቹ በምናከብረው እሴታችን ላይ እንዲቀልዱ መፍቀድ አንችልም። መለሰ እያደራጀ የሚልካቸው የይስሙላ ሽማግሌዎች የተከበረውን ሽምግልና አዋርደዋልና አጥብቀን ልንቃወማቸው ይገባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## ስዩም መስፍን በኬንያ ወደምትገኝ አንዲት ከተማ ባደረገው የግል ጉዞ ከፍተኛ መጠን ያለው የህዝብ ገንዘብ አባክኗል ተባለ

ስዩም መስፍን ከሁለት ሳምንትበፊት ዘ ግሬት ሌክስ ኦፍ ኪሱሙ ከተባለው የኬንያ ዩኒቨርሲቲ በአፍሪካ የሰላም ግንባታ ላደረገው አስተዋጾ በሚል የክብር ዶክትሬት ዲግሪ እንዲሰጠው መደረጉ በበርካቶች ዘንድ አነጋጋሪ ሆኖ ሰንብቷል።

ከውጭ ጉዳይ ምንጮች ዘግይቶ የደረሰን መረጃ ደግሞ ወደ ኬንያ የሄደበት ምክንያት ብቻ ሳይሆን አካሄዱም አነጋጋሪ እንደሆነ ይጠቁማል። የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሄዶ እንዲቀበል ጥሪ የተደረገለት ስዩም፣ በዜናው ከመደሰቱ የተነሳ፣ ለጉዞው የራሱ የሆነ አውሮፕላን እንዲዘጋጅለት አዟል። የኪሱሙ አውሮፕላን ማረፊያ ግን፣ ለምሳሌ መለስ ዜናዊ የሚጠቀምበትን አይነት፣ ትልቅ አውሮፕላን ማስተናገድ እንደማይችል ሲታወቅ፤ አነስተኛ የሆነና መቶ ሃምሳ ተጓዦችን የሚይዝ አውሮፕላን ይዞ ከነአጃቢዎቹ ተጉዟል።

የአውሮፕላኑ፣ የእሱና የአጃቢዎቹ የሆቴል ወጪ፤ እንዲሁም ባረፈበት ሆቴል ለዩኒቨርሲቲው ሰዎች ያደረገው ግብዣ ተደማምሮ ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ ተደርጓል። ከምንጮቻችን የደረሰን መረጃ ቁጥሩን 250 ሺህ ዶላር ላይ ያኖረው ሲሆን፤ ይህ ዜና እስከተጠናከረበት ጊዜ ድረስ ከሌላ ምንጭ ለማረጋገጥ አልቻልንም።

ይሁን እንጂ፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰራተኛ በተፃፈ እና ከዚህ ቀደም ባወጣነው ሪፖርት መሰረት፤ ስዩም መስፍን ወደ ውጭ አገር በተጓዘ ቁጥር ይዞ የሚሄደው ገንዘብ ምንም አይነት ቁጥጥር አይደረግበትም። በዛም አኳኋን ሚኒስትሩ ወደ ጎረቤት አገራት እንኳ በሚያደርገው የአንድ ቀን ጉዞ በአስር ሺሆች የሚቆጠር ዶላር ይዞ እንደሚሄድ እና ሲመለስም ምንም የሂሳብ ማወራረድ እንደማይካሄድ ታውቋል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916

## የተከበሩ ወ/ሮ አና ጎምዝ በዋሽንግተን ዲስ ለኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዝን በተደረ የገንዘብ ማሰባሰብ ዝግጅት ያደረጉት ንግግር ግንቦት 15 2002 ዓ.ም (ክፍል 3 የመጨረሻ ክፍል)

ይህ የሚያስታውሰኝ አገሬ በ አምባገነኑ ሳላዛር አገዛዝ ስር በነበረችበት ወቅት ሳላዛር እኛ ፖርቹጋላውያን ዘገምተኞች እና ለዴሞክራሲ ዝግጁ አለመሆናችንን እናም እንደማያስፈልገን ይነግረን ነበር። ነገር ግን ለዴሞክራሲ ስርአት ዝግጁ መሆናችንን የሳላዛርን አገዛዝ ከመሰረቱ በመፈንገል አምባገነኖችን አሳይተናቸዋል። እናም እጅግ በጣም በጣም እርግጠኛ ነኝ ኢትዮጵያውያንም የመለስን አፋኝ አገዛዝ ከስረ መሰረቱ መንግላችሁ እንደምትጥሉት።

ብልሆች፣ የቆረጡና በዓላማቸው የፀኑ ሰዎች እንዳሏችሁ አውቃለሁ፤ በዚህ አጋጣሚም ለብርቱካን ሚደቅሳ ያለኝን አክብሮት እገልፃለሁ። ከዚህ በፊትም እንደገለፅኩት የሷ መታሰር ምርጫው ነፃና ፍትሃዊ እንደማይሆን ማረጋገጫ ነው። ምርጫው ነፃና ፍትሃዊ ቢሆን ኖሮ እሷም ከእስር በወጣች፤ ተዳድራም ባሸነፈች ነበር።

በብርቱካን አማካይነትም በመለስ ዜናዊ እስር ቤቶች ለሚገኙ በርካታ ወንዶችና ሴቶች ያለኝን አክብሮት እገልፃለሁ። እንዲሁም በእነኚሁ እስር ቤቶች የደረሰባቸው ስቃይና መከራ ሳይበግራቸው ትግላቸውን በብልህነት ለቀጠሉት ያለኝን አድናቆት እገልፃለሁ። በብልሃት መታገል ማለት ደግሞ መተባበር ማለት ነው - ሌላ መንገድ የለውም።

መለስ ከፋፍሎ ነው እየገዛ ያለው፤ መከፋፈል የሁልጊዜ ስልቱ ነው። ሁሉም አምባገነን አገዛዞች ከፋፍለው ነው የሚገዙት። ስለዚህም ከዚህ ጨቋኝ አገዛዝ ለመገላገል እናንተ ኢትዮጵያዊያን መተባበር አለባችሁ የምለው።

የመለስ ዜናዊ ወንጀሎችን አይቶ እንዳላዩ ለማለፍ ለሚፈልጉ አውሮፓውያን የተቃዋሚዎች መበታተን ከህሊና ተጠያቂነት ማምለጫ ሰበብ ሆኗቸዋል። “አህ!!! ምን ማድረግ ይቻላል? ተቃዋሚዎች እንደሆነ ተበታትነዋል” ይላሉ። ተቃዋሚዎች አውሮፓም ውስጥ ቢሆን የተከፋፈሉ ናቸው፤ በእኔም አገር ውስጥ እንደዚያው ነው።

የዲሞክራሲ ሂደት እራሱ ልዩነቶችንና መከፋፈልን ይፈጥራል፤ ሆኖም በወሳኝ ወቅት እና አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ሲኮን አብሮ መቆም ይገባል፤ ስለዚህም ነው ስለመተባበር ደጋግሜ ልነግራችሁ የፈለግሁት። ልዩነቶችን ከአምባገነኑ ሥርዓት መወገድ በኋላ ለማስተናገድ የማቆየትን አስፈላጊነት በተመለከተ በ1999 ዓም ተናግሬ የነበረውና አሁን ያለምዘውድ ያስታወሰችንን ዛሬም ልደግመው በጣም እፈልጋለሁ። ይህንን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲና ፍትህ እስኪሰፍን ድረስ በአገራዊ አጀንዳ ማበር ሲቻል ነው።

በ1997 መለስ ዜናዊ በዘር ላይ የተመሰረተ ግጭት ለመፍጠር እንደምን ያሉ የጥላቻ ንግግሮችን እንደተጠቀመ አስታውሳለሁ። አደገኛ የሆኑ በዘር ላይ የተመሰረቱ ግጭቶችን ለማስነሳት ምን ያህል እንደለፋ አስታውሳለሁ። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ይህንኑ ጨዋታ በእሱ እጅ እንደተጫወቱት አስታውሳለሁ። በተለይ አቶ ልደቱን አስታውሳለሁ፤ ዛሬም በአሁኑ የምርጫ ዘመቻ ይህንኑ ጨዋታ በመለስ ዜናዊ መዳፍ ውስጥ እየተጫወተው ነው። አስታውሳለሁ፤ ያኔ እሱ የከረሩ ነገሮችን እየተናገረ ተቃዋሚዉን ወገን የአማራ የበላይነት አጀንዳ ለማስመሰል ጥሯል። ይህ ደግሞ የኦሮሞ ሕዝብ አብላጫ በሆነበትና ብዙ ሌሎችም ባሉበት ስለ አንድ ወገን ለይቶ መናገር ልዮነትን እንደሚያሰፋ ግልጽ ነበር። አስታውሳለሁ፤ አቶ ልደቱ አክራሪ ነበር። ለምን እንዲህ እንደሆነ አሁን ገብቶኛል። ያኔ በመለስ እጅ እየተጫወተ ነበር፤ አሁንም ጫወታውን እንደቀጠለ ነው። እናም እንዲ ያለ ወጥመድ ውስጥ እንዳትወድቁ ላሳስባችሁ እወዳለሁ። ለዚህ ደግሞ መድሃኒቲ ዲሞክራሲና ፍትህ በኢትዮ ጵያ እስኪሰፍኑ ድረስ ልዩነቶቻችሁን ወደጎን አድጋችሁ በጋራ በመነሳት ነው።

ወዳጆቼ፤ ለረዥምም ሰዓታት ስላስጠበቅኋችሁ ስብሰባው ረዝሞባትኋል። አንድ ተጨማሪ ትዝታ ብቻ ልናገር። በአገሬ በሊዝቦን ከተማ የታወቀ የመፃህፍት ኤግዚቢዥን አለ። ኢትዮጵያን በጥልቀት ያጠና ፓርቹጋላዊ አንትሮፖሎጂስት ስለ ኢትዮጵያ ድንቅ የሆነ መጽሃፍ ጽፎ በምረቃው እለት ስለኢትዮጵያ አንዳች ነገር ሰምተው ለማያውቁ ሆኖም ግን ስለዛች አገር ለማወቅ ለሚጓጉ ፓርቹጋላዊያን የመናገር ክብር ተሰጠኝ። መጽሃፉ የጥንት የፓርቹጋልና የኢትዮጵያ ግኑኝነት ላይ ያተኮረ ቢሆንም እኔ ግን የዛሬዋን ኢትዮጵያ ምን እንደምትመስል፤ ለዲሞክራሲና ፍትህ የምታደርጉትን ተጋድሎ ለአገሬ ሰዎች ለማስተዋወቅ ተጠቀምኩበት። እዚህ በዲያስፖራ ያላችሁ ኢትዮ ጵያዊያን አንዱ ሥራ በየአላችሁበት አገር ያሉ መሪዎች ስለኢትዮ ጵያ ኢንዲያውቁ እዚያ ፍትህ ስትረገጥ ፊታቸውን አዙረው በቸልታ እንዳያልፉት ማድረግ ነው። አውሮፓውያንና አሜሪካዊያን ኢትዮጵያያን አንባገነንነትን ለማስወገድ በእርግጥም ቆርጠው መነሳታቸውን፤ ትግላቸውንም እዳር ለማድረስ ብቃት ያላቸ መሆኑን ማመን ይፈልጋሉ።

እኔ ትተባበራላችሁ፤ በብልህነት ትታገላላችሁ፤ በየጊዜዉም የበለጠ ብልህነት የተሞላው ስልት ትጠቀማላችሁ ብዬ አምናለሁ። መለስ ዜናዊ የገነባውን የዝምታ ግንብና የመረጃ አፈናን ለምስበር እንደምትሞክሩ አውቃለሁ።

በአምስት ወራት ይሁን በአምስት ዓመታት በኋላ እንደሆነ አላውቅም እንጂ አዲስ አበባ ውስጥ ነፃነትን እንደምናከብር አንዳችም ጥርጣሬ የለኝም

አመሰግናለሁ፤

## ዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በህጋዊ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እና አባላቶቻቸው ላይ የሚያደርገውን ጥቃት ቀጥሏል

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እና ቤተሰቦቻቸው ላይ የሚያደርገውን ጥቃት እንደቀጠለ ነው፤ ከግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት በፊት እንደነበረው ሁሉ ግድያ፣ እስር፣ ድብደባና እንግልት ቀጥሏል።

በደቡብ ክልል ውስጥ በደራሼ ልዩ ዞን የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ሰብሳቢ የሆኑ ግለሰብ ባለቤት መገደላቸውን እና ሁለት ልጆቻቸውም በጥይት ተመተው መቁሰላቸውን የፓርቲው ዋና ጸሃፊ አቶ ማሙሸት አማረ ለአሜሪካ ድምጽ ራድዮ በሰጡት ቃል ገልጸዋል። ወ/ሮ አማረች ገላኔ የተባሉት የልጆች እናት ደሰነች በሚባል አካባቢ የህዝብ የምርጫ ታዛቢ እንደነበሩ እና የምርጫው ሂደት ትክክል እንዳልሆነና እየተጭበረበረ መሆኑን ለአካባቢው የፖሊስ ኮማንደር ባመለከቱ ጊዜ ከግለሰቡ ዛቻ እንደደረሰባቸው አቶ ማሙሸት ተናግረዋል።

እሁድ ግንቦት 22 ቀንም ወ/ሮዋ ከልጆቻቸው ጋር ተቀምጠው ቡና እየጠጡ ባሉበት የፖሊስ ኮማንደሩ ጠባቂ የሆነ ሰው ተኩሶ እንደገደላቸው ገልጸዋል። የእናቲቱ ሁለት ልጆችም በመጮሃቸው፣ የአስር አመቱ ልጅ ሁለት እግሮቹን በጥይት የተመታ ሲሆን፤ የአስራ ሁለት አመት ልጃቸው ደግሞ በጀርባዋ ላይ የመታት ጥይት በሆዷ ወጥቷል።

አቶ ማሙሸት በሌሎች አካባቢዎች በሚገኙ የድርጅታቸው አባላቶች ላይም እንግልት እና እስር እየደረሰ መሆኑን፤ እንዲሁም የመግስት አገልግሎቶችን እንደሚከለከሉ አስታወቀዋል።

የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ መሪ ዶ/ር መረራ ጉዲና በበኩላቸው ከምርጫ ተውኔት ዋዜማ ጀምሮ እስከ ማግስቱ ድረስ በሺዎች የሚቆጠሩ ታዛቢዎቻቸው ሲታሰሩ እና ሲዋከቡ እንደቆዩ ለአሜሪካ ድምጽ ሬድዮ ተናግረዋል። ባሁኑ ሰዓትም ወደ ሃምሳ የሚጠጉ አባላቶቻቸው እስር ላይ እንደሚገኙ እና አንዳንዶቹም የአምስት ወይም የስድስት ወር እስር እየተፈረደባቸው እንደሚገኝ አስታውቀዋል። የግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት እንዳበቃ ሁለት የኦህኮ አባላት በጥይት ተመትተው መገደላቸው ይታወቃል።

## በፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅ የሚመራው የሽማግሌዎች ቡድን የመለስ ዜናዊን ማስፈራሪያዎች ለመድረክ አመራር አባላት እያስተላለፈ መሆኑ ታወቀ

ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅን ግንቦት 18 ቀን ወደ ቢሮው በመጥራት የመድረክ ፓርቲ አመራሮች የግንቦት 15ቱን የምርጫ ተውኔት ውጤት እንዲቀበሉ እንዲያግባቧቸው ማዘዙን አዲስ ነገር ኦንላይን የተባለው ድረ-ገጽ ዘግቧል።

ፕሮፌሰሩም የመድረክ አመራር አባላት የምርጫውን ውጤት ለመቀበል ከተስማሙ እንደማይታሰሩ በመንገር ዘረኛው አምባገነን የሰጣቸውን ማስፈራሪያ መልእክት አስተላልፈዋል። የመድረክ ፓርቲ አመራሮች ግን ማስፈራሪያውን እንዳልተቀበሉ እና ሽማግሌ ተብየዎቹ የመለስ ተላላኪዎች ለመሆን በመፍቀዳቸው ማዘናቸውን ድረ-ገጹ አክሎ ገልጿል።

መለስ ዜናዊ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የምርጫውን ተውኔት ውጤት ቢቀበሉ ምእራባውያን መንግስታት እያሰሙ ያሉትን ተቃውሞ ያቆማሉ ብሎ እንደሚያምን ድረ-ገጹ ምንጮቹን ጠቅሶ ዘግቧል። የልደቱ አያሌው ፓርቲ የምርጫውን ተውኔት ውጤት እንደሚቀበል ያስታወቀ ሲሆን፤ የወያኔው አገዛዝም መድረክ ከዚሁ ጎራ እንዲሰለፍ ይፈልጋል።

የመድረክ መሪዎች የማስፈራራሪያ መልእክቱን አልቀበል ሲሉ፣ አምባገነኑ መለስ የፕሮፌሰር ኤፍሬምን ቡድን መልሶ በመላክ ችግር አለባቸው በሚባሉ ጥቂት ቦታዎች ምርጫው እንዲደገም ሊፈቅድ እንደሚችል መልክት መላኩን አቡጊዳ የተባለው የዜና ድረ-ገጽም ዘግቧል። የመድረክ አመራር አባላት ይህንንም እንዳልተቀበሉ እና ምርጫው እንዳለ ይደገም በሚለው አቋማቸው ላይ መርጋታቸው ታውቋል።

የግንቦት 7 ንቅናቄ ከሁለት ሳምንት በፊት ዝግጅቱ ተውኔት ያደረገው መሰረታዊ ነገር በስልጣን ላይ ያለው አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ሆኖ ሳለ፤ አገዛዙ ባለበት ምርጫው ቢደገምም እውነተኛ ለውጥ እንደማይመጣ ሲናገር ቆይቷል።

## የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር የግንቦት 15ቱን የምርጫ ተውኔት አወገዘ፤ የትብብር ጥሪም አቀረበ

የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ወይም ኦነግ ባወጣው መግለጫ የግንቦት 15ቱን የምርጫ ተውኔት ሃሰተኛ እና ሽፍጥ የሞላበት ብሎ ያወገዘ ሲሆን፤ የወያኔን የውጭ ደጋፊዎችም ያሳፈረ ብሎታል።

ግንባሩ ከዚህ ቀደም ከገዢው ፓርቲ ጋር የነበረው ግንኙነት የወያኔ አገዛዝ አምባገነናዊ ስለመሆኑ እና ለዴሞክራሲ፣ ለሰብአዊ መብት መከበር፣ ለነፃነት እና ለህግ የበላይነት ሃሳቦች የተገዛ አለመሆኑን ለማሳየት በቂ ማስረጃ እንደነበረ ጠቅሷል። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ከዚህ ምርጫ ውስጥ ምንም ብዥታ የሌለበት ፍጹም አምባገነናዊ አገዛዝ ሆኖ ወጥቷልም ብሏል።

ኦነግ በዚሁ መግለጫ፥ ነፃነት፣ ፍትህ፣ ዴሞክራሲ እና የህግ የበላይነት በኢትዮጵያ እንዲሰፍኑ ለሚታገሉ ሃይሎች፣ የትግሉ ሁኔታ ካሁን በተሻለ ግልጽ እና ምቹ ሊሆን የሚችልበት ጊዜ እንደሌለ ጠቅሶ፤ እርስ በርስ መናቆሩ ቀርቶ የመተባበር እና ትኩረታችንን ህዝባችንን ከአምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ነፃ ለማድረግ በሚደረገው ትግል ላይ የማኖሩ ጊዜ አሁን ነው ብሏል።

ግንቦት 7 የነፃነት፣ የፍትህ እና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ግንቦት 17 ቀን ባወጣው መግለጫም የትብብር ጥሪን ማስተላለፉ ይታወሳል። በዛ መግለጫ፥ "የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ: "የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!" የሚል ነው።" ብሏል።

## የዛሬ አምስት አመት ሰኔ አንድ ቀን ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በንጹሃን ዜጎች ላይ የፈጸመው ጭፍጨፋ ታሰበ

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የዛሬ አምስት አመት በአዲስ አበባ በሚገኙ ንጹሃን ዜጎች ላይ የፈጸመው ጭፍጨፋ በአለም ዙሪያ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን በዛሬው እለት ታስቧል።

ፌስቡክ በተባለው መገናኛ ድረ-ገጽ ላይ የሚሳተፉ በርካታ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች፣ ሰኔ አንድን ለማስታወስ በሚል ሳምንቱን ሙሉ በግል ገፃቸው ላይ የሻማ ምስል ለጥፈው ሰንብተዋል። የዝግጅት ክፍላችን ባልደረባ "አንረሳም" የሚል ጽሁፍ የተፃፈበትን የሻማ ምስል ከለጠፉ ወጣቶች ውስጥ ለአንዱ የኢ-ሜይል መልክት ልካ ነበር። ወጣቱ በላከው መልስም፥ "ሰኔ አንድ 1997ትን መቼም ቢሆን አልረሳውም። ምክንያቱም በስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ መቀመጫውን ለመጠበቅ ሲል የት ድረስ ሊሄድ እንደሚችል የተገነዘብኩት ያን ቀን ነው።" ብሏል። "በዛን ቀን በንጹሃን ዜጎች ላይ የተደረገው ግድያ...ለህዝቡ ተጠያቂነት በማይሰማው አምባገነናዊ አገዛዝ ስር እንደምኖር ጥብቅ ማስታወሻ ሆኖኛል" ሲልም አክሏል።

### አንፈራም

የሞተ ሞት አይፈራም
ሽብሬ የመቱሽ ለታ
እኛም ሞተን ነበር ለካ

ነፍሳችን ከነፍስሽ ጋራ
የተሳሰ'ረችበት
የኢትዮጵያዊነት ገመድ
አንድ አድርጎናልና
አንቺ ስትሞቺ አብረንሽ
እኛም ስንኖር አብረሽን
አንድ ላይ ኗሪ ነንና
ለዘላለም እንቆያለን
እጅ ለእጅ ተያይዘን
ኢትዮጵያውያን ሆነን

ሞተሽ ስላነቃሽን
ደምተሽ ስላስተማርሽን
እንደሞትን አንቀራትም
ግፍ እንደ-ተ-ሰ-ራብን
ረግጠው እንዳዋረዱን
እንቡጥ አበቦቻችንን
ቀጥፈው እንደጣሉብን

አንፈራም
የሞተ ሞት አይፈራም
እናሸንፋለን እህት አለም
ኖረን እናኖርሻለን

ድላችን ለአንቺም ድልሽ
ሳቃችንም ያንቺ ሳቅሽ
ያለን ሁሉ ያንቺ ነው
የሚኖረንም እንደዛው
ሞተሽ ስላነቃሽን
ደምተሽ ስላስተማርሽን

አንቺ ስትሞቺ አብረንሽ
እኛም ስንኖር አብረሽን
ፍቅር ያስተሳሰረን
የአንድ እናት ልጆች ነንና
እናሸንፋታለን እታለሜ
ኖረን እናኖርሻለን

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org